# በኤች አይ ቪ የምክር አገልግሎትና ምርመራ ዙሪያ ምን አዲስ ነገር አለ?

## ተጨማሪ ምስጢራዊ የምርመራ ቦታች

የኦንታሪዮ መንግስት በቅርቡ 24 ተጨማሪ ምስጢራዊ የምርመራ ቦታችን በመክፈት ጠቅላላ የምርመራ ቦታችን ቁጥር ወደ 50 ያደረሰ ሲሆን በግዛቱ ውስጥ በሚገኙ ብዙ ቦታችም ምስጢራዊ የምርመራ ቦታችን አስፋፍቷል፡፡ የኤችአይቪ ምርመራን ለማድረግ ጊዜው ወይም ልምዱ የሌላቸው ሐኪሞች ባለጉዳዮቻቸውን ወደ ሕዝባዊ ጤናና ፆታ ክሊኒክ ወይም ወደ ምስጢራዊ የምርመራ ማዕከላት ለመላክ ይችላሉ፡፡ የምስጢራዊ ምርመራ ቦታችን አድራሻና ስልክ ለማግኘት የኤድስ ሆት ላይንን በሚከተሉት ቁጥሮች ደውለው ይገናኙ፡፡
416-392-2437 ወይም 1-800-668-2437 የፈረንሣይኛ መስመር፡ 1-800-267-7432

### የኦንታሪዮ ምስጢራዊ የምርመራ ቦታች የት ይገኛል?

22 በህዝባዊ ጤ፣ና ክፍሎች

16 በማኅበረሰብ የጤ፣ና ማዕከላት

4 በአዋላጆች ዘንድ (ለደንበኞቻቸው ግልጋሎት ብቻ)

3 በፆታዊ ጤ፣ና ማዕከላት

5 በሌ፣ሎች ቦታችና ሆስፒታልነ የወጣቶች ኤ፣ጀንሲ፣ነ ሁለት የአቦሪጅናል

## ተጨማሪ ተለዋዋጭ ምርመራች

የጤና ሚኒስቴር እና ሎንግ ተርም ኬር በምስጢራዊ የምርመራ ቦታችና ለህዝባዊ ጤናና ፆታዊ ክሊኒኮች እንዲሁም ተመሣሣይ አገልግሎት በሚሰጡ የማኅበረሰብ ጤና ማዕከላት በመገኘት በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የምርመራ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ በፓይንት ኦፍ ኬር ምርመራ ከኤችአይቪ ነፃ የሆኑ ሰች ውጤታቸውን በተመረመሩ በደቂቃች ውስጥ እንዲያውቁ ይደረጋል፡፡ በፓይንት ኦፍ ኬር ምርመራ ኤችአይቪ የተገኘባቸው ሰች ውጤታቸው ደረጃውን በጠበቀ ላቦራቶር እንደገና መረጋገጥ ያለበት ሲሆን ውጤታቸውን ለማግኘትም እስከ 2 ሣምንታት መጠበቅ ይኖርባቸዋል (ማስታወሻ፡ ውጤት የመቀበያ ጊዜው በግዛቱ ውስጥ ከቦታ ቦታ ይለያያል) በተጨማሪ ም የህዝባዊ ጤንነት ላቦራቶሪ የምርመራ ፎርሙ የሚመረመረው ሰው ቫይረሱ ሊደበቅበት በሚችልበት ጊዜ /ብሽቃሳቄብ ቅስቄሽቄሳ/ ውስጥ ያለ መሆኑንነ ምልክት የሚያሳይ መሆኑን እና ለቫይረሱ የተጋለጡ መሆኑን በሚያሳይበት ጊዜ በምርመራ ናሙናች ላይ የፒ24 አንቲጀን ምርመራ ያንሂዳል፡፡

## ሊኖሩ ስለሚችሉ ሥጋቶች የበለጠ ዕውቀት

አሁን ከዚህ በታች የተመለከቱትን አውቀናል፡፡ ይኸውም፡-

- ወጣት ሴቶች (ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆነ) በኤችአይቪ የመያዝ አጋጣሚያቸው ከትልቅ ሴቶች የበለጠ መሆኑንና የዚህም ምክንያት የማህፀን በር ህዋሶች (ኣስቁቁቋ) እስከ 18 አመት ዕድሜ ድረስ ሙሉ በሙሉ ስለማያድጉ መሆኑን
- የሙኮሳል ማምብሬን (ቂበሰቄቋሮቁ ቂስቂሯቄሮቃስ) ጤንነት በሌሎች በወሲብ የሚመጡ ኢንፌክሽኖች መኖርነ በሴቴ የሆርሞን መጠንነ በቅባት ማነስ እንዲሁም በሚቆረቁሩና መሰል ነገሮች በመጠቀም ሳቢያ የሚጎዳ መሆኑን
- አነስተኛ የሆነ ቫይረስ ሎድ (ባሽቄሮቁ ቁቄሮሳ) የኤችአይቪን የተላላፊነት መጠን ሊቀንሰው ይችላል እንጂ አያጠፋውም፡፡ የአንቲ ቫይራል (ፀረ ቫይረስ) መድኃኒቶች ሁልጊዜም ኤችአይቪን በመራቢያ አንላት ውስጥ ለመቆጣጠር አይቻላቸውም፡፡ ግለሰቡ ሌላ በወሲብ የሚተላለፉ ኢንፌክሽን ናለበት ስጋቱ ከፋ ያለ መሆኑን
- እንደ መርፌ ከመሰሉ የሕክምና መገልገያች ሌላ እንደ መቀቀያች ማጥለያችኖ ውሃነ አልኮልነ የማጤሻ ትቦ የመሳሰሉ ዕቃችን መጋራትም በኤችአይቪ የመያዝ ዕድሉን ሊያሰፋ የሚችሉ መሆኑን

## ማኀበራዊ ሁኔታች/ሥጋቶችን በተመለከተ የተሻለ መረዳት

የሰች ጥንቃቄ የተሞላበት ወሲብን ለመፈፀምና መድኃኒት ለመጠቀም የሚኖራቸው ችሎታ እንደ ድህነትነ የቤት ውስጥ የኃይል አለመጣጣምነ የዕፅና አልኮል የመጠቀም ሁኔታ እንዲሁም መገለል በመሳሰሉ የተለያዩ ከጤና ጋር የተያያዙ ማኀበራዊ ጉዳዮች ሲነኩ/ሲጎዱ ይታያል፡፡

Ontario

ሰች የሚገጥሟቸው ጉዳዮች በዕድሜነ በፆታዊ እውቀትነ በባህልና በዝርያ ጭምር ይለያያሉ:: ውጤታማ የሆነ የመከላከል የምክር አገልግሎት እነዚህን ሁሉ ጉዳዮች መዳሰስ ይኖርበታል:: (ስለሕዝብ ጉዳዮች የተደረጉ አጫጭር ውይይቶችን ለመመልከት አባሪ 2ን ይመልከቱ)

## የሌሎች በወሲብ የሚመጡ ኢንፌክሽኖች እና የሂፓታይትስ ሲ ምርመራ ጠቀሜታ

ለኤችአይቪ ከተጋለጡ ሰች ውስጥ ጥቂት የማይባሉት ለሌሎች በወሲብ ለሚመጡ ኢንፌክሽኖች እና ለሂፒታይትስ ሲ ጭምር የተጋለጡ ናቸው:: ማንኛ ውም ለኤችአይቪ ምርመራ የሚመጣ ሰው ለሌሎች በወሲብ ለሚመጡ ኢንፌክሽኖች እና ለሂፒታይትስ ሲ ጭምር የተጋለጠ መሆኑ ሊነገረው እና ምርመራ እንዲያደርግም ጥያቄ ሊቀርብለት ይገባል::

## ለኤች አይ ቪ ምርመራ የሚፈለገው ጊዜ

የኤች አይ ቪ ቅድመ ምርመራ የምክር አገልግሎት በ15-20 ደቂቃች ውስጥ ሊከናወን ይችላል:: ነገር ግን እንደ ተመርማሪው የእውቀት መጠንና ሌሎች ፍላጎቶቹ ይህ ጊዜ ሊለያይ ይችላል::

## ለወደፊት የትዳር/የፍቅር አጋሮች የመግለፅ ህጋዊ ግዴታን በተመለከተ

ባለፉት ዓመታት አያሌ ሰች ለወሲብ ጓደኞቻቸው ኤችአይቪ ያለባቸው መሆኑን ሳያሳውቁ ጓደኞቻቸውን ለኤችአይቪ በከፍተኛ ሁኔታ አጋልጠው ወሲብ በመፈፀማቸው በወንጀል ተፈርዶባቸዋል:: ኤችአይቪ ያለባቸው መሆኑ በምርመራ ተረጋግጦ የተነገራቸው ሰች አሁን ማንኛውንም ዓይነት ለኤችአይቪ የሚያጋልጥ የወሲብ ግንኙነት ከፈፀማቸው በፊት ለወሲብ ጓደኞቻቸው ቫይረሱ ያለባቸው መሆኑን መንገር አለባቸው:: የወሲብ ጓደኞቻቸው ግንኙነቱን ለመፈፀም ፈቃደኛ መሆናቸውን ማረጋገጥ ቢችሉም እንኳን ጥንቃቄ ያልተሞላበት ወሲብ በመፈፀማቸው ከኃላፊነት አያመልጡም:: ሕጉ ሌሎች የቫይረሱን መተላለፍ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ሁኔታችን በሚመለከት እስከ አሁን ግልፅ አይደለም:: ሕጋዊ የመግለፅ ግዴታን በተመለከተ ለበለጠ መረጃ የኦንታሪዮ ኤችአይቪ እና ኤድስ ክሊኒክ (ኦንታሪ ዮ) (ኤችኤኤልሲኦ) በስልክ ቁጥር 416-340-7790ነ 1-888-705-8889 ወይም በድህረ ገጽ ብብብ.ሻሮቁሰቄ. ቁቄሸ ይገናኙ::

## ከቋንቋ ጋር ለተያያዙ ችግርች እርዳታ

የኤድስ ሆት ላይን በ18 ቋንቋች መረጃ የሚሰጥ ሲሆን በምክር አገልግሎት ጊዜ ባለሙያው ከባለጉዳዩ ጋር አንድ ዓይነት ቋንቋ የማይናገር በሚሆንበት ጊዜ ለአስተርጓሚነት አገልግሎት በቂ የሰው ኃይል አለው:: ከኤችአይቪ ምርመራ ጋር በደንብ የሚተዋወቁ ሲሆን እጅግ በጣም ጥሩ የመረጃ ምንጭም ናቸው:: (የኤድስ ሆት ላይን ቁጥሮች 416-392-2437 ወይም 1-800-668-2437ነ የፈረንሣይኛ ቋንቋ መስመር ቁጥር: 1-800-267-7432)

### በጃንዋሪ 2008 የኤይስ ሆት ላይን በሚከተሉት ቋንቋች አገልግሎት ሰጥቷል::

አርመንኛ
ቤንጋል
ናንቶኒዝ
እንግሊዝኛ
ፊሊፒኖ
ፈረንሣይኛ
ሀን
ሂንዲ
ማንዳረን
ፓርቹጊዝ
ሩስኪ
ሲንሃሊዝ
ስፓኒሽ
ስዋሂሊ
ታይዋንኛ
ታሚል

## ለጓደኛ ማሣወቅን በተመለከተ እርዳታ

የምክር አገልግሎት ሰጪች አስቸጋሪ ጉዳዮችን በተ መለከተ ምክር በሚሰጡበት ጊዜ ይረዳቸው ዘንድ የኤድስ ቢሮ ለጓደኛ ማሣወቅን በተመለከተ ዝርዝር የሆነ መመሪያ በመሥራት ላይ ይገኛል::

## ሌሎች መመዘኛች

በጤና ሚኒስቴር እና ሎንግ ተርም ኬር የተዘጋጀው «የኤችአይቪ የምክር አገልግሎትና ምርመራ መመሪ ያ» ጥንቃቄ የተሞላበት ወሲብ መመዘኛችኖ ለምክር አገልግሎት የተዘጋጁ ጠቃሚ ነጥቦች እና ፖዘቲቭ የምርመራ ውጤትን በመስጠት ዙሪያ ያሉ ምክሮችን የመሳሰሉ እያሉ መመዘኛና ነጥቦችን የያዘ ነው::

በ«SayYesToKnowing.ca» ስለ ምርመራ የበለጠ ይወቁ::

Amharic Catalogue No. CIB-6153291 March/08 © Queen's Printer for Ontario